# ቲቢ (የሳንባ ነቀርሳ)

ቲቢ በባክቴሪያ ምክንያት የሚከሰት በሽታ ነው። በአብዛኛው ጊዜ ቲቢ በሳምባዎች ላይ የሚከሰት ሲሆን በሌሎች የሰውነት ክፍሎች ላይም ያጋጥማል (ለምሳሌ በአጥንቶች፣ የሊንፍ እባጮች ፣ ወይም በአዕምሮ)።

- ቲቢ በህክምና የሚድን በሽታ ነው
- በኖርዌይ የቲቢ ምርመራ እና ህክምና በነጻ ይሰጣል

## በቲቢ እንዴት ሊያዙ ይችላሉ?

ቲቢ በሳንባው ውስጥ ያለበት ሰው በሚያስል ወይም በሚያስነጥስ ጊዜ ባክቴሪያው በአየር ውስጥ በአይን በማይታዩ ትናንሽ ጠብታዎች አማካኝነት ይሰራጫል። እነኝህን በአየር ላይ የተሰራጩ ጠብታዎች ወደ ውስጥ ያስገቡ ሰዎች በባክቴሪያው ይያዛሉ። የቲቢ ባክቴሪያ በቀላሉ አይሰራጭም ቅርበት ካለ ሰው ጋር፣ ለምሳሌ ከቤተሰብ አባል፣ የመያዙ አጋጣሚ ግን የተለመደ ነው።

## የቲቢ ምልክቶች

የቲቢ የተለመዱ ምልክቶች ቀጥሎ የተዘረዘሩት ናቸው፦

- ከ 2 – 3 ሳምንታት ወይም ከዚያ በላይ የቆየ ሳል
- የምግብ ፍላጎት መቀነስ
- የክብደት መቀነስ (በጣም ቀጭን መሆን)
- የአቅም መቀነስ እና ድካም ስሜት
- ለረዥም ጊዜ ትኩሳት ሲኖርዎ
- የሌሊት ላብ
- በጉሮሮ፣ በብብት እና ብሽሽት ውጫዊ ክፍል ላይ የሚታይ እብጠት ወይም መጓጎል



ከእነኝህ ምልክቶች አንዱ ወይም ከዛ በላይ የታየበት ማንኛውም ሰው ዶክተር ጋር ሄዶ መመርመር አለበት

## አስገዳጅ የሳንባ ነቀርሳ (ቲቢ) ምርመራ

የሳንባ ነቀርሳ በብዛት ከሚገኝባቸው አገሮች የሚመ   እና በኖርዌይ ውስጥ ከሶስት ወር በላይ የሚቆዩ ሰዎች የሳንባ ነቀርሳ ምርመራ እንዲያደርጉ ይገደዳሉ   የምርመራ ዘዴው እነደየ ሰ   ሊለያይ ይችላል ይህም  እንደ የሳንባ   ክስ  ይ፣ የደም ምርመራ፣ የቆዳ ምርመራ ወይም ለበሽታው እንዴት እንደተጋለ   የሚጠይ   ጥያ  ዎችን ሊያካትት ይችላል።







የምርመራው   ላማ በተቻለ ፍጥነት በሽታ የተያዘወን ሰው መለየት ፣ ህክምናው እንዲሰጥ እና የበለጠ እንዳይሰራጭ ለመከላከል ነው።